ንግድ-ቻምበር

# የዜና መጽሄት

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የመረጃና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ የዜና መጽሄት

ቁጥር 172 ከየካቲት 15—30 ቀን 2011 ዓ.ም.

## በውስጥ ገጾች


- የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ … ገጽ 2
- ሁለቱ አገሮች በቁም ከብቶች … ገጽ 3
- ፕሬዚደንቱ የናይጄሪያን … ገጽ 3
- የቱርክ ባለሀብቶች … ገጽ 4
- ምክር ቤቱ ከኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ … ገጽ 4
- የግንዛቤ ማስጨበጫ … ገጽ 5


## ዜና ቻምበር

## ፎረሙ የሁለቱን ሀገራት የኢኮኖሚና የንግድ ግንኙነት የበለጠ እንደሚያጠናክረው ተገለፀ






የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከኬንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከኬንያ ብሄራዊ የንግድ ምክር ቤት እና ኢንዱስትሪ ጋር በመተባበር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ እና የኬንያው ፕሬዚደንት ኡሁሩ ኬንያታን ጨምሮ የሁለቱ አገሮች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት እና የግል ኩባንያዎች ተወካዮች የተገኙበት የኢትዮጵያ-ኬንያ የንግድና ኢንቨስትመንት ፎረም የካቲት 22 ቀን 2011 ዓ.ም. በስካይ ላይት ሆቴል አዲስ አበባ አካሄደ፡፡

የፎረሙ ዋና አላማ የንግዱ ማህበረሰብ በሁለቱ ሀገራት ያሉትን የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች እንዲያውቁና በጋራ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሁለቱን ሀገራት የኢኮኖሚና የንግድ ግንኙነትና ትብብር የበለጠ ለማጠናከር ነዉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በፎረሙ መክፈቻ ንግግራቸው እንደገለፁት የኢትዮጵያን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እና የንግድና ኢንቨስትመንት ትብብሯን ከጎረቤት አገሮች ጋር በተለይም ከኬንያ ጋር ለማስቀጠል ባለፉት 10 ወራት መንግስታቸው ጠንክሮ እየሰራ ነው፡፡ በሁለቱ አገሮች መካከል ሰላምና ኢኮኖሚን ለማሳደግ ድንበር ተሻጋሪ ንግድና ኢንቨስትመንት በጣም ጠቃሚ እንደሆነም አስገንዝበዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከኬንያ በተለይም በቱሪዝም ዘርፍ ልምድና እዉቀት ማግኘት የምትፈልግ መሆኗን በመጥቀስ በአግሮ ኢንዱስትሪ፣ ቴክስታይልና ቆዳ በመሳሰሉት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች እንዲሁም

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለክብርት አምባሳደር ሙሉ ሰለሞን የእንኳን ደስ ያለዎ የእራት ፕሮግራም እና የሽኝት ስነ-ስርዓት አካሄደ፡፡

ክብርት አምባሳደር ሙሉ ሰለሞን በጀርመን የኢትዮጵያ ባለ ሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሆነው በመሾምዎት እንኳን ደስ ያለዎት ለማለት እወዳለሁ፤ ሲሉ ንግግራቸውን የጀመሩት የምክር ቤቱ ፕሬዚደነት ኢንጂነር መለዓኩ እዘዘው፤ የዝግጅቱ ዓላማ ክብርት አምባሳደር የምክር ቤታችን ፕሬዚደንት በነበሩበት ወቅት ላሳዩት አመራር እና ላስገኙት ውጤት እውቅናን ለመስጠት የተሰናዳ ብቻ ሳይሆን፤ በመንግስት የተጣለባቸውን ኃላፊነት እና አደራ በላቀ አፈጻጸም እንደሚወጡም እምነታችንን ለመግለጽ ጭምር ነው ሲሉ አክለዋል፡፡

አያይዘውም የምክር ቤታችን ፕሬዚደንት በነበሩበት ዓመታት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በሚፈለገው መልኩ እንዲያድግ እና የውጪ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እንዲቻል ካሳዩት ከፍተኛ ጥረት ባሻገር ባለዎት ሙያ፣ ዕውቀትና ክህሎት ብሎም ተሞክሮ የተጣለብዎትን ኃላፊነትም በተሻለ መልኩ እንደሚወጡ እምነታችን ነው ብለዋል፡፡

በሌላም በኩል ሁለቱን አገራት በንግድ እና ኢንቨስትመንት የበለጠ ለማስተሳሰር በሚያደርጉት ጥረት



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትም ከጎናቸው እንደማይለይ አረጋግጠዋል፡፡ በፕሮግራሙ ላይ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችም ተገኝተዋል፡፡

## ፎረሙ የሁለቱን ሀገራት....

ከገጽ 1 የዞረ

በኢነርጂና በአቬሽን የኢንቨስትመንት እድሎች ላይ ለሚሰማሩ የኬንያ ባለሀብቶች በሯ ክፍት እንደሆነ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

በመሰረተ-ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክት ሁለቱን አገሮች ብሎም ምስራቅ አፍሪካን ለማገናኘት በተስማሙት መሰረት ኬንያ አሁንም አጋርነቷን ጠብቃ እየሰራች መሆኗን ያስታወሱት የኬንያው ፕሬዚደንት በበኩላቸው በምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ በቤቶች ግንባታ፣ በማኑፋክቸሪንግ እና በጤና ጥበቃ የኢንቨስትመንት እድሎች ላይ በሽርክና የሚሰሩ የኢትዮጵያ ባለሀብቶችን ጋብዘዋል፡፡

የሁለቱ ሀገራት መሪዎች ያሏቸውን የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች በማስተዋወቅና በጋራ በመጠቀም የሁለቱን ሀገራት የኢኮኖሚና የንግድ ግንኙነትና ትብብር የበለጠ ለማጠናከር ጠንክረው እንደሚሰሩም ቃል ገብተዋል፡፡

የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ፣ የኢትዮጵያና የኬንያ ግንኙነት በጋራ ባህልና ጠንካራ ታሪክ ላይ የተመሰረተ መሆኑን በማስታወስ የሁለቱን አገሮች የቢዝነስ፣ ኢንቨስትመንት፣ ግብርና እና መሰረተ-ልማት ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ፋይዳ ያለውን ይህን ፎረም ለማካሄድ በወሰዱት ርምጃ የሁለቱን አገሮች መንግስታት አመስግነዋል፡፡

በፎረሙ ላይ ስለሁለቱም ሀገሮች የንግድና ኢንቨስትመንት እምቅ ሀብቶች እና እድሎች ላይ የፓወር ፖይንት ገለፃ እና የፓናል ዉይይት ተደርጓል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ በፓናል ዉይይቱ ወቅት የኢትዮጵያና የኬንያ የኢኮኖሚ እድገትን ከግል ዘርፉ እይታ አንፃር አስመልክተው እንደተናገሩት የኬንያ የግሉ ዘርፍ ጠንካራ ከመሆኑ አንፃር በኬንያ ኢኮኖሚ እድገት ላይ የመሪነቱን ሚና በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ እያበረከተ ይገኛል፡፡ በአፍሪካ ቀጠናዎች እና አህጉር ያሉ የገበያ እድሎችን በመጠቀም የተሻለ በመሆኑም ኢትዮጵያ እንደ አፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጠና(ACFTA) የመሳሰሉ የገበያ እድሎችን ወደፊት በአግባቡ ለመጠቀም እንድትችል ከኬንያ ጋር በአጋርነት በመስራት ልምድና እውቀት ልትወስድ ይገባታል፡፡ የግሉ ዘርፎች ሁለቱም አገሮች ቅድሚያ በሚሰጧቸው የማኑፋክቸሪንግ፣ ኤይሲቲ፣ መሰረተ-ልማት በመሳሰሉት የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ በሽርክና ቢሰሩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑም አብራርተዋል፡፡ ዋና ፀሐፊው አክለው እንደገለጹት የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር በሀገሪቱ ላይ እያደረጉት ያለው አዲስ አመራር የግሉን ዘርፍ የበለጠ የሚያነቃቃ እና ኢንቨስትመንትን የሚስብ በመሆኑ የግሉ ዘርፍ አንቀሳቃሾች በአንድ ላይ በመሆን መንግስት ለሚያደረገው የፖሊሲ ተሃድሶ/መሸሻል/ ውጤታማና ጠቃሚ ሊሆን የሚችል ፕሮፖዛል ሰርተው ማቅረብ ይገባል፡፡

በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክ፣ በኢነርጂ፣ በፋይናንስ እና በአገልግሎት ሰጪ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ከ300 በላይ የኢትዮጵያ ኩባንያዎች 200 ከሚሆኑ የኬንያ አቻዎቻቸው ጋር የአቻ ለአቻ ስብሰባ አካሂደዋል፡፡

# ሁለቱ አገሮች በቁም ከብቶች  እርባታና ድለባ ላይ ተባብረው ቢሰሩ ትርፋማ እንደሚሆኑ ተጠቆመ



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) በኢትዮጵያ የአውስትራሊያ አምባሳደር ፒተር ዶይለን የካቲት 19 ቀን 2011 ዓ.ም. በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

በግንኙነታቸውም ወቅት አውስትራሊያ እና ኢትዮጵያ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ የቁም ከብቶች አርባታ፣ ድለባ፣ በስጋ እና በወተት ውጤቶቻቸው እንዲሁም በቆዳ ምርቶቻቸዉ ላይ እሴት በመጨመር አብረው በሚሰሩበት አግባብ እና በሁለቱ አገሮች የንግዱ ማህበረሰብ መካካል ስለሚኖረው የቢዝነስ ግንኙነት ላይ ተወያይተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካም ሆነ በአለም ደረጃ ከፍተኛ የቁም ከብቶች ቁጥር ያላት አገር ቢሆንም ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እያገኘች እንዳልሆነ የጠቆሙት ፕሬዚደንቱ አውስትራሊያ በዘርፉ ያላትን ከፍተኛ የእዉቀትና ልምድ ደረጃ በተለይም የስጋና የወተት ምርታማነትን በማሳደግ እና እሴት በመጨመር የሚመረትበትን አሰራር መማር እንደምትፈልግ ተናግረዋል፡፡

ፕሬዚደንቱ ጨምረው የአውስትራሊያ ባለሀብቶች ከኢትዮጵያ አቻዎቻቸው ጋር ተባብረው በዚህ እና እንደ ቆዳ፣ ቡናና ሰሊጥ ባሉ ሌሎችም የግብርና ነክ ዘርፎች እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ቢሰማሩ ትርፋማ ስለሚሆኑ ኢትዮጵያ ያሏትን የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች አስመልክቶ መረጃ ለአውስትራሊያ የንግዱ ማህበረሰብ እንዲያስተላልፉ እና ባለሀብቶቹ መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ አምባሳደሩን ጠይቀዋል፡፡

አምባሳደር ፒተር በበኩላቸው አውስትራሊያ በቁም ከብቶች እርባታና ድለባ፣ በወትትና በስጋ ምርቶች ምርታማነት ላይ በመሰማራት ለበርካታ ዘመናት እየሰራች ያለች አገር መሆኗን በመጥቀስ የሁለቱ አገሮች የቢዝነስ ማህበረሰብ በጋራ ቢሰሩ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በቀጣይ የኢትዮጵያ እና የአውስትራሊያ የንግድ ምክር ቤቶች ተቀራርበው በመስራት የሁለቱን አገሮች የንግድ ማህበረሰብ የቢዝነስ ግንኙነት በሚያጠናክሩበት ረገድ እና ሁለቱ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ በሚሆበኑበት መንገድ ዙሪያም መክረዋል፡፡

# ፕሬዚደንቱ የናይጄሪያን አምባሳደር ተቀብለው አነጋገሩ



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) በኢትዮጵያ የናይጄሪያ አምባሳደር ባንኮለ አደአዬ የተመራውን ሶስት የልዑካን ቡድን አባላት የካቲት 18 ቀን 2019 ዓ.ም. በፅ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

የሁለቱን አገሮች የንግድ ማህበረሰብ ግንኙነት ከማጠናከር፣ ንግድና ኢንቨስትመንት ከማስፋፋት እና የጋራ ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን ከማሳደግ አንፃር ኢምባሲውና ምክር ቤቱ አብረው በሚሰሩበት አግባብ ላይ ተወያይተዋል፡፡

ኢትዮጵያ እና ናይጄሪያ በአፍሪካ አህጉር ከፍተኛ የሰው ሀይል፣ በርካታ የግብርና ውጤቶች እና የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች ያሏቸው አገሮች በመሆናቸው የንግዱን ማህበረሰብ ግንኙነት በማጠናከር ለጋራ ጥቅም አብረው ቢሰሩ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ በውይታቸው ላይ በሰፊው ተወስቷል፡፡

# የቱርክ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ከ2.5 ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስት እያደረጉ መሆኑ ተገለፀ



የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) የቱርክ አምባሳደር ያፕራክ አልፕን የካቲት 14 ቀን 2011 ዓ.ም. በፅ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

አምባሳደሯ እንደተናገሩት ከ180 በላይ የሚሆኑ የቱርክ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ተሰማርተው ከ2.5 ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስት እያደረጉ መሆኑን አስታውሰው በሁለቱ አገሮች የንግዱ ማህበረሰብ መካከል ያለው የቢዝነስ ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱንና ወደፊትም የበለጠ እንዲጠናከር የበለጠ መስራት ይገባል፡፡

ፕሬዚደንቱ በበኩላቸው እንደተናገሩት በርካታ ኢትዮጵያዉያኖች የቱርክን ምርቶች ተጠቃሚ እንደሆኑ እና የቱርክ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር እያመጡ ያሉ እንዲሁም በርካታ የስራ ዕድል በመፍጠር አስተዋፅኦ እያደረጉ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተገንብተው በስራ ላይ የዋሉ እንደሆኑና አሁንም በርካታ ፓርኮች በመገንባት ላይ እንዳሉ በማብራራት የቱርክ ባለሀብቶችም በግንባታው ላይ ቢሳተፉ አዋጪ ይሆናል፡፡ በኢትዮጵያ ቡና፣ ሰሊጥና ስጋ የመሳሰሉ ምርቶች ተጨማሪ እሴት እንዲያገኙ በሚያስችል የግብርና ኢንቨስትመንት ላይ ቢሰማሩ ትርፋማ እንደሚሆኑም ኢንጂነር መልአኩ አክለው ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም የቱርክ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ በሚያደርጉት የቢዝነስ እንቅስቃሴያቸው ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በጋራ ለመፍታት በየጊዜው እየተገናኙ አብረው በሚሰሩበት ሁኔታ ላይ፣ የሁለቱ አገሮች የንግዱ ማህበረሰብ እና የቢዝነስ ግንኙነት በሚጠናከርበት አግባብ እንዲሁም ሌሎች የሁለትዮሽ ጉዳዮችም ላይ ዉይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

# ምክር ቤቱ ከኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ተቋም ጋር ውይይት አካሄደ

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ ከኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ተቋም ከፍተኛ ሀላፊዎች ጋር በዓለም አቀፍ የጨርቃ ጨርቅ ማሽነሪ አፍሪካ 2020 ኤግዚቢሽን የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የካቲት 13 ቀን 2011 ዓ.ም. በተቋሙ አዳራሽ ተወያዩ፡፡

ዋና ፀሀፊው በምክር ቤቱ እና በህንድ ዓለም አቀፍ የጨርቃ ጨርቅ ማሽነሪ ኤግዚቢሽን ማህበረሰብ (India International Textile Machinery Exhibitions Society /ITME Society/ ትብብር እ.ኤ.አ ከየካቲት 14- 16 / 2020 አዲስ አበባ ስለሚዘጋጀው ዓለም አቀፍ የጨርቃ ጨርቅ ማሽነሪ አፍሪካ 2020 ኤግዚቢሽን አስመልክቶ ምክር ቤቱ ባቀደው የድርጊት መርሃ-ግብር ላይ ለመወያየት እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ከአይቲኤም ማህበረሰብ /ITME Society/ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ከተፈራረመ በኋላ ምክር ቤቱ ያከናወናቸውን እና እያከናወናቸው ያሉ ተግባራቶችንም በዝርዝር ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ተቋም ዋና ድሬክተር አቶ ስለሺ በበኩላቸው እንደገለፁት ኤግዚቢሽኑ በምክር ቤቱ በኩል እንዲካሄድ ተቋሙ ቀደም ሲል የራሱን ጥረት ያደረገ መሆኑን በማስታወስ ኤግዚቢሽኑ በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆን እንዳለበትና በዘርፉ ላይ የተሰማሩ አገር በቀል ድርጅቶችም ተመርጠው ቴክኖሎጂዎቻቸውን ቢያቀርቡ ለወደፊቱ የፈጠራ ስራቸው ሊያበረታታቸው ይችላል፡፡



ሁለቱ ወገኖች በተለይም ኤግዚቢሽኑ ስለሚካሄድበት አዳራሽ፣ በኤግዚቢሽኑ ላይ ስለሚቀርቡ የጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ አይነቶች፣ ስለአገር ዉሥጥ ተሳታፊዎች አመራረጥ፣ ኤግዚቢሽኑ ለንግዱ ማህበረሰብ ስለሚተዋወቅባቸው ሁኔታዎች፣ በግሙሩክ ነክ እና በርካታ ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ዉይይት ያካሄዱ ሲሆን ኤግዚቢሽኑ ሙሉ በሙሉ ለታቀደለት ዓላማ በስኬት እንዲከናወን ከወዲሁ ጀምረው የተቻላቸውን ሁሉ ለማድረግ ተስማምተዋል፡፡

## የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ተዘጋጀ

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ የማህበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ግምሩክ ኮሚሽን ጋር በመተባበር የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች እና ኢ-ሲኤምሲ አገልግሎት በሚል ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለነጋዴዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም አዘጋጀ፡፡

የግንዛቤ ማስጨበጫው ዋና አላማ እንዴት የተመረጠ የኢኮኖሚ አንቀሳቀሽ እንደሚኮንና የሚያስገኘውን ጥቅሞች ለግሉ ዘርፍ ግንዛቤ በመፍጠር የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮገራም፣ ኢ-ሲኤምሲ አገልግሎት እና በዘርፉ የተከናወኑ ምርጥ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የፓወር ፖይንት ገለፃ ተደርጎ ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም (Authorized Economic Operators Program) ቅድሚያ የፍተሻ አገልግሎት እንደሚያስገኝ፣ የቁጥጥር ስራውን ቀላልና ቀልጣፋ እንደሚያደርግ፣ ቀልጣፋ የዶክመንት ምርመራ እና ፈጣንና ቀላል የድክላሪሲዮን ምዝገባ አገልግሎት እንዲኖር ብሎም የተቀላጠፈ የግምሩክ ስርዓት እነዲኖር እነደሚያደርግ ተገልጿል፡፡

በዓለም አቀፉ የንግድና የሸቀጥ/ምርት ሰንሰለት ያላቸው አምራቾች፣ አስመጭዎች፣ ላኪዎች፣ ትራንዚተሮች፣ አጋጋዦች፣ የመካዘን ባለቤቶች፣ አከፋፋዮች፣ የደረቅ ወደቦች እና የመሳሰሉት ድርጅቶች የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ውሥጥ ለመካተት ማመልከት እንደሚችሉና ለአገር ኢኮኖሚ ባላቸው አስተዋፅኦ፣ በፋናንስ አቅማቸው፣ በህግ ተገዥነታቸው፣ በሀብት አመራርና የመረጃ አያያዝ ስርዓታቸው እና በመሳሰሉት መስፈርቶች እየተመዘኑ ደረጃ እንደሚሰጣቸው በፕሮግራሙ ላይ ተብራርቷል፡፡

በእለቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ላይ ከተለያዩ የግል ድርጅቶች የተውጣጡ ተወካዮች ተሳትፈውበታል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ማዕከል

አድራሻ፡- +251-115-31-10-15

**ዋና አዘጋጅ፡- ደበበ አበበ**
**አዘጋጆች፡- ዮሴፍ ተሾመ**
**ጥበቡ ታዬ**
**ካሜራ፡- ያሬድ አባቡ**
**ፕሮቶኮል፡- ሲሳይ አስታጥቄ**

**አድራሻ፡-**
**ስልክ-፡- +251-115-54-09-93**
**ፋክስ፡-+251-011-5517699**
**ኢሜል፡- ethchamb@ethionet.et**
**ድረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com**